# የይለፍ ሰነድ (ሊሴፓሴ) አሰጣጥ ሁኔታ - Laissez-Passer Application

## በግንባር ቀርበው ለሚያመለክቱ

- አመልካች በአካል ቀርቦ ለዚህ አገልግሎት ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ መረጃዎችን በተሟላ መልኩ ተሞልቶ ሲቀርቡ /በሁለት ኮፒ/፣
- ኢትዮጵያዊነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ መረጃዎች የተረጋገጠ የልደት ሰርተፊኬት፣ የቀድሞ ፓስፖርት ኮፒ፣ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ ወዘተ... ሲቀርብ፣
- የግራና የቀኝ እጅ አመልካች ጣቶች አሻራ ሲሰጥ፣
- አራት ፎቶግራፍ መጠኑ 3x4 cm የሆነ፣
- ከሚኖሩበት ኢሚግሬሽን ወይም ከፖሊስ የተሰጠ የምዝገባ ሰነድ /ዜግነትን ቢሚያሳይ መልኩ/ ማረጋገጫ ወረቀት፣
- ክፍያ ሲፈጸም፣

## የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች በሌሉባቸው አገሮች ቀርበው ማመልከት ለማይችሉ

- የሊሴፓሴ መጠየቂያ ቅጽ በሁለት ቅጂ ተሞልቶ ሲቀርብ፣
- ሊሴፓሴ እንዲሰጠው በጽሑፍ ማመልከቻ ሲያቀርብ፣
- ኢትዮጵያዊነቱን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ማስረጃዎች /የተረጋገጠ የልደት ሰርተፊኬት፣ የቀድሞ ፓስፖርት ኮፒ ወዘተ/ ሲያቀርብ፣
- ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው የአሻራ መስጫ ፎርም ላይ የግራና የቀኝ እጅ አመልካች ጣቶች አሻራ በፎርሙ ላይ በአካባቢው ፖሊስ ፊት ቀርቦ ሲነሳና አሻራው የግለሰቡ መሆኑ በፖሊስ ጣቢያው የጽሁፍ መግለጫ ሲሰጠው ወይም በፐብሊክ ኖታሪ ወይም ተመሳሳይ ሕጋዊነት ባለው አካል ሲረጋገጥና ይኸውም በሚኖሩበት ሀገር በየሀገራቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፣
- አራት ፎቶግራፍ መጠኑ 3x4 cm የሆነ ሲያቅርብ፣
- በደንቡ መሠረት የሊሴፓሴ ክፍያውና የፖስታ መላኪያውም ጭምር ሲልክ፣

## ክፍያ

- 415 የስዊድን ክሮነር
- ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መላክ ይኖርበታል፡፡
- ክፍያ በፖስታ መላክ አይቻልም፡፡

## ክፍያ የሚፈፀምበት

Bank Giro No. 521-8235 write message instead of OCR No. Or
Seb Bank IBAN No. SE575000 0000 0527 7110 6248, Bic-Code ESSESESS

## ማሳሰቢያ

- በስዊድን ነዋሪ የሆኑ የተዘጋጀላቸውን የይለፍ ሰነድ/ሊሴፓሴ የመመለሻ አድራሻ የተዘጋጀበት ባለ 104 ክሮነር ስታምፕ የተለጠፈበት የተዘጋጀ ፖስታ አብሮ መላክ፣
- ከስዊድን ውጭ የሚኖሩ የተዘጋጀላቸውን የይለፍ ሰነድ/ሊሴፓሴ የመመለሻ አድራሻ የተዘጋጀበት ባለ 118 ክሮነር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ ያለው ኢንተርናሽናል ኩፓን መላክ ይኖርባቸዋል፡፡
- ኤምባሲው ለአገልግሎት ከሚጠይቀው የክፍያ መጠን እንዲሁም የባንክ ኮሚሽንና የፖስታ መላኪያ ገንዘብ ወጪ የሚፈፀም ማንኛውም በትርፍ ገቢ የሆነ ገንዘብ የማይመለስ መሆኑን እንገልፃለን፡፡